# ለትውስታ ይብቃው ወልደጻዲቅ



ይብቃው ወልደጻዲቅ
Yibkaw Woldetsadik

መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ይብቃው ወልደጻዲቅ በኢሕአፓ ዘመኑ የዛሬ 6 ዓመት *“ፍፁም ነው እምነቴ የከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ”* ነሲቡ ስብሐት መስከረም 2007 ዓ.ም. መጽሐፍ ከገጽ 236 እስከ 240 ይህ ተዘግቦለታል ይህንን ብሏል።

“ከከፍተኛ 15 ቀበሌ 27 በሕይወት ያለ ጊዜ ካተረፋቸው ወጣት የኢሕአፓ ልጆች አንዱ ይብቃው ወ/ፃዲቅ ነው። ከይብቃው ጋር በድርጅት ጉዳይ ባልገናኝም በጣም እንዋደዳለ። አንዳንዴ እቤቴ ሰብሰብ እያልን እሱ፣ የመስኪ እህት ጌጤ አናወጥና ኤልሳ የልጅነት ፍቅረኛሞቹ መስኪና ማሙሽን ያዝናኑናል። 1969 ዓ.ም. የፋሲጋ በዓል ዋዜማ ይብቅቲ ቤት መጥቶ ስንጫወት “እባክህ መስኪን ደውለህ ጥራትና አብረን እንጫወት” ብሄው ደውሎ እንደመጣ ደቂቃም ሳይቆይ መስኪ በቤት ልብሷ እጇ ላይ ያለውን ሊጢን በደንብ ሳትታጠብ ቀሚሷ የተንጠባጠበ ሊጥ እንደያዘ ስትበር ትመጣለች።



ይብቃው ሳቁ ሊቆም አልቻለም “ምን ያህል ብትወጂው ነው ልብስ መቀየር ያቃተሽ?” እያለ እምባው እስኪፈስ ይስቃል። መስኪ እንደገባች ቁጭ አልኩበት አልጋዬ ላይ ተጠግታኝ ቆም ብላ የራስ ፀጉሬን እያሻሸች “እህ እማዬ እኮ ለፋሲጋ ዳቦ አቡኪ ብላኝ አሁንም አልጨረስኩም ሸውጃት ነው ስሮጥ የመጣሁት” ትለዋለች። ቀጠል አርጋም የይብቃውን ሳቅ በሳቅ እየመለሰችለት “ማሙሽዬ እንደሆነ ሁለመናዬን ነውና የሚወደው አትጨነቅ” እያለች “አይደል ማሙሽዬ?” በማለት ማረጋገጫ ድጋፌን ከፊቴ አነበበች።  “በይ ጨርሺና ነይ ደሞ ቸኩለሽ እንዳታብላሺው” ብለናት የፋሲጋን ዋዜማ አብረን አመሸን። ይብቃው እስከዛሬ መስኪን ሲያነሳ ሁኔታዋ ትዝ ይለዋል።

የይብቃው ወንድም በላይ እጅግ በጣም የታወቀ ሁሌም ስለ ኢሕአፓ ሰው ሳይፈራ ቦታ ሳይመርጥ እንዳወራ ነው። መሠረተ ትምህርት ሲያስተምር ለእናቶች ስለ ኢሕአፓ እንደሰበከ ይጨርሰዋል። በቤታቸው አጠገብ ያለውን የአዲሲቱ ቡና ቤት ሴት እህቶቻችንን ቡናና ሻዩን እየጠጣ ስለ ኢሕአፓ እየቀሰቀሰ  የኢሕአፓ ደጋፊ በማድረግ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል። በላይ አንዳንዴ ከድርጅቱ አሠራር ውጭ እየሄደ በሚያደርገው ፊት ለፊት ሰበካ ማንም ሊያቆመው ስላልቻለ በቀበሌው እጅግ በጣም ታወቀ። የቀበሌ 27 አቶ በዛብህና ሌሎች በላይን ዋናው የኢሕአፓ መሪ ድረስ አድርሰውታል። በላይ ለኢሕአፓ ካለው ፍቅር የሚያደርገው ቢሆንም በዚህ መልኩ መቀጠሉ ለሱም ሆነ ለሌሎች አስጊ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል በመባል በወሬና በዝና ወደ ምንወደው ‘አሲምባ’ ተላከ። በቀይ ሽብር መከራው ወደ ‘አሲምባ’ በመውጣቱ ሊያገኙት ባይችሉም ቤተሰቡን በሙሉ አሰቃይተዋል። ወንድሙን ዓለማየሁን አረመኔው ከፈለኝ በግል ጥላቻ እስኪተላ ገርፎታል።
ይብቃው በእጃቸው የገባው እንዲሁ የመግደል መብታቸው ከተገፈፈ በኋላ ዘላለማዊ ቀይ ሽብራቸው በቃችሁ በተባሉ ማግስት እየመረራቸውና እየተናደዱ በተቀበሉበት ወቅት ነበርና ቀጣይ እስራቸውን ተከናንቦ በ1978 ዓ.ም. ከስምንት ዓመት እስር በኋላ የተፈታው የኢሕአፓ ጀግና ትዝታው እነሆ፦

*“እኔ ሁሉም ነገሮች እየተምታቱብኝ የነበረው በ1969 ጳጉሜን 5 ነው። ቀኑ ትዝ ይለኛል ወደ 12 ሰዓት ላይ የአዲስ አበባን ሰማይ ደመና ወሮት ነበር። ያኔ ደርግ መስከረም 2 ቀንን ለማክበር በፍርሃት እየተንቀሳቀሰ ነበር። እኛ ደግሞ የአሸናፊነት ስሜት ቢኖርም ውስጣችን ችግር በችግር ነበር። ቀስ በቀስ ችግሩ እየተባባሰ በመምጣቱ ለደርግ ስለተመቸው የቀይሽብር ዘመቻውን በሰፊው ሕዝብ ላይ ለማካሄድ አስቻለው።*

*‘እስከ የካቲት 1970 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባና በናዝሬት ስንቀሳቀስ ቆይቼ ሁሉም ነገር ብልሽትሽት ሲል በአንድ የድርጅቱ አባል አማካኝነት በአሰብ በኩል አድርጌ ጣሊያን ለመግባት የካቲት 6 ቀን 1970 ዓ.ም. ደሴ ገብቼ የይለፍ ከደሴ ለማግኘት 3 ቀን ቆይቼ በመከራ ሎግያ ላይ ዘመድ ለመጠየቅ መግባት እንደማይቻል በደርግ ወታደሮች ተነግሮኝ እንደገና በናዝሬት በኩል ከመንግሥት እርሻዎች ሠራተኛ ጋር ከሰላ እንድሄድ አድርጌ በጉዞ ላይ እያለሁ አንባ ላይ ከምሽቱ 4 ሰዓት መኢሶን የሆነ የጥበበ ባንቲ የትምህርት ቤት ጓደኛ በአብዮት ጥበቃ አስከብቦ በቁጥጥር ሥር አዋሉኝ። እዚያ ለ3ወር ቆየሁ።*

*‘ግንቦት 10 ቀን አዲስ አበባ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 34 እስር ቤት መጣሁ። በማግስቱ ቀንና ለሊቱን የእነ ከፈለኝ አጨብጫቢዎች ሁሉም ነገር እንዳከተመና ሁሉም ሰው ወደ አብዮቱ ካምፕ እንደገባ ሲነዘንዙኝ ዋሉ አደሩ። በኋላ አንደኛው እነ ሰሎሞን በሰማሁ ሁሉንም ነገሮች እንዳጋለጡ ሲነግረኝ ከአወጣሁ ካወረድሁ በኋላ ቤቴ የቀበርኩት መሳሪያ እንዳለ ነግሬአቸው ሰፍ ብለው ይዘውኝ ወጡ።*

*‘ግንቦት 12 ቀን 1970 የነከተማ ግሩፕ ቤት ይዘውኝ መጡ። መሳሪያ የማሳያቸው መስሏቸዋል እኔ ግን ሁሉም ተሰፋዬ ስለተሟጠጠ ስሮጥ እንዲመቱኝ አስቤ ስለወጣሁ በካዛንቺስ አጂፕ ጀርባ ወደ ቤቴ መግቢያ በአለው ቀጭን መንገድ ሮጥሁ። ግርማ ኮሚኒስት በያዘው ክላሽ ሊመታኝ ሲል አረመኔው ገራፊ ደምሴ ከኋላዬ እኔን ለመያዝ ይሮጥ ስለነበር መምታት አልቻለም። እኔም አንድ አጥር ዘልዬ ላመልጥ ስሞክር ከፊትም ከኋላም ሲመጡብኝ አንድ ትንሽ ኩሽና/ማዕድ ቤት ዘልዬ ገብቼ የሙቀጫ ዘነዘና አገኝሁና ከፊት ለፊቴ ደምሴን አግኝቼ አናቱን ልለው ስል ከተማ በያዘው ሽጉጥ ከወገቤ በታች በአንድ ጥይት መትቶኝ ወደኩ።*

*‘ከዚያም አንስተውኝ 34 እስርቤት ግርፊያ እሚካሄድበት ሕንፃ ጀርባ በረንዳ ላይ ወረወሩኝ። የእነሱ አጨብጫቢዎች እየመጡ ይሰድቡኛል። ይረግጡኛል። በተለይ ከናዝሬት ከፈለኝ ይዟቸው የመጡ ጭንቅላቴ ላይ እየወጡ ሲረጋግጡኝ*

*እሰድባቸውና ‘ኢሕአፓ ያቸንፋል፣ ባንዳዎች’ እያልኩ መፈክር አወርድባቸው ነበር። የነበሩት አብዛኛው እስረኛም ሁኔታውን አልወደዱልኝም። ምክንያቱም “የቀረውን ሞት እንደገና ሊቀሰቅስብን መጣ” በማለት ይመስለኛል። ያለምንም ህክምና ለ21 ቀን እዚያው በረንዳ ላይ ከአስቀመጡኝ በኋላ የሲሳይ ምንዳ ቁስል እየሸተተ በመምጣቱ ምክንያት ከእሱ ጋር ወስደው እስረኛው ጋር ቀላቀሉን።*

*‘ከ6ወር በኋላ ነገሮችም ወደ ገራፊዎቹም እየዞረ እየመጣ በመሆኑ ዋስ ጠርቼ ለህክምና ወጣሁ። ህክምናዬን ከጨረስኩ በኋላ እንደገና ለምርመራ ተጠርቼ የማዕከላዊ መርማሪዎች መርምረው ግማሻችንን ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ሲልኩን ወር ከቆየሁ በኋላ በ1972 ዓ.ም. ከርቸሌ ወርጄ በ1978 ዓ.ም. ለመፈታት ቻልኩ።*

*‘የካቲት 6 ቀን 1970 ዓ.ም. ነው ከአዲስ አበባ መልቀቅ የጀመርኩት። እስከዛሬዋ ዕለት እግዜር ለእኔ ያደረገልኝ በችግራችን፣ በስቃያችን ተካፋይ እንደነበር እንዲታወቅ እፈልጋለሁ።*

*‘ሁሉም ነገሮች ጭልምልም ብሎብኝ ስለነበር በድኔ ብቻ ነበር የሚራመደው። የዚያ ለት ወደ ደሴ ለመሄድ ማደር ያለብኝ መርካቶ አካባቢ ስለነበረ አልጋ በጠዋት መርካቶ ሹፌሮች ቡና ቤት ይገኝአለሁ። መርካቶ ይጨናነቅ የነበረው እረጭ ከማለቱም በላይ ሁሉም ሰው በፍርሃት ተጨናንቆ ነበር። ሰዓት እስኪደርስ እየተዟዟርኩ ከቆየሁ በኋላ ሻንጣዬን ይዤ ወደ አንድ ሰዓት ከምሽቱ ሲደርስ ወደ ሆቴሉ ገባሁ። ሻንጣዬን መኝታ ክፍል አስቀምጬው ወጣሁ። ትንሽ እንዲመሽልኝ ልዟዟር ብሞክር በጣም አስፈሪ በመሆኑ እዚያ አልጋ እያዝኩበት ቡና ቤት ገብቼ አንድ ወንበር ላይ ስቀመጥ አንድ ቀይ ልጅ መጥታ ‘ምን ልታዘዝ’ ስትለኝ፤ ‘ፋንታ’ ስላት ደንግጣ ምንም ሳታናግረኝ ቢራ አቀረበችልኝና ለሷም ይዛ መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች። እኔም በድኔ ትክ ብሎ እያየት ዝም ብዬ መጠጣት ጀመርኩ።*

*‘ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ቤቱ በአብዮት ጥበቃ ተከበበ። ጠባቂዎቹ ግቢውንና ቤቱን ማተራመስ ጀመሩ። ‘አይዞህ ዝም ብለህ ተቀመጥ’ አለችኝ አጠገቤ ተቀምጣ ቀደም ብላ የጀመረችውን ቢራ እየጠጣች። ክፍሎቹንና ቤቱን ከፈተሹ በኋላ ቡና ቤቱ ውስጥ ያለነውን ሰዎች መታወቂያችንን ከተመለከቱ በኋላ የቤቱን ኃላፊ ይዘውት ወጡ። ከ30 ደቂቃ በኋላ በአካባቢው የጥይት እሩምታ ተሰማ፤*
*‘ወይ ጉድ እነኚህ ሰዎች እያበዱ ናቸው’ ስትለኝ ምንም አልመለስኩላትም። ሰዓቱ ገና ስለነበር ከዚያው አልተነቃነኩም ቀስ እያለ ፍርሃት ይሁን ቅዝቃዜው ሰውነቴ በጣም ከመቀዝቀዙ በላይ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ።*

*‘ምነው ቢራውን ጠጣ’ ብላኝ ሁለተኛውን ከፈተችልኝ።*

*‘እኔም ምንድነች? ሰላይ ነች በማለት በጣም ፈራኋት። ቡና ቤቱ የነበሩት ወጣ ወጣ እያሉ ወዲያው ጭር ሲል*

*‘ይህን ጊዜ ወንድሜን ገለውት ይሆናል’ ብላ፤*
*‘እናንተ የዘመኑ ልጆች የሚገርም ስቃይ ላይ ናችሁ’ አሁንም ምንም አልተናገርኩ።*
*በጣም ብዙ ካወራችልኝ በኋላ ‘የት ነው የምታድሪው?’ አልኳት*
*‘አሁን እቤት እንዴት ይኬዳል?’ ብላ ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰችልኝ።*
*‘ለምን አብረን አናድርም?’*
*‘እሺ’ ብላኝ ትንሽ ከቆየን በኋላ ተያይዘን ገባን። የቢራውን አላስከፈለችኝም።*

*‘ስለ ኢሕአፓ፣ ስለመኢሶን፣ ስለመንግስት ስታወራ ከቆየች በኋላ ‘ለካ ነገ መንገደኛ ነህ’ ብላ ተኛች። እኔም ብዙ እያሰላሰልኩ ከቆየሁ በኋላ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ። ሊነጋጋ ሲል ለመነሳት ስል እሷም ነቃችና ‘ይቅርታ’ ብላ ሰዓቷን ስታይ ገና 11 ሰዓት በመሆኑ ትንሽ እንድቆይ ጠይቃኝ*

*‘እኔ ኮ ሂሳብ አልከፈልኩሽም’ ስላት*
*‘የምን’ አለችኝ፤*
*‘የቢራውንም ያንቺንም’።*
*‘አይዞህ የቢራውን እኔ ነኝ የጋበዝኩህ ሌላ ደግሞ የምትከፍልበት ምንም ምክንያት የለም ይልቅ’ ብላ ትንሽ ካለቀሰችና ካሰበች በኋላ የአንገት ሀብሏን አውልቃ ሰጠችኝና*
*‘እግዜር ይጠብቃችሁ’ አለችኝ።*
*‘ሳላውቀው እንባዬ ጉንጬ ላይ ፈሰሰ። አሁንም ሳስበው ያስለቅሰኛል። ሀብሉን በመጨረሻም የወሰዱት የ34ቱ አውሬዎች ናቸው።”*

ይብቃው ወልደጻዲቅ ጠንካራ የኢሕአፓ ታጋይ የነበረና እስከ እለተ ሞቱ ኢሕፓን አፍቃሪ፣ ያ ዘመን ከአፉ የማይጠፋ ወንድማችን ነበር። ስለ ሕይወቱና ስለ ኢሕአፓ ዘመን ባይታተምም በመጽሐፍ መልክ መጻፉን አውቃለሁ። ሁኔታዎች ከተመቻቹ ከያ ትውልድ ተቋምና ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በመተባበር ለዕትመት ይበቃለት ዘንድ እንሞክራለን።
ያ ትውልድ ተቋም ለቤተሰቦቹ፣ ለዘመድ ወዳጆቹ፣ ለትግል ጓዶቹ ብርታትና መጽናናትን እግዚአብሔር ይሰጥልን ዘንድ እንመኛለን።
ነፍስ ይማር
ነሲቡ ስብሐት የያ ትውልድ ተቋም ቦርድ ሰብሳቢ መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም. (September 7, 2020)